Freebirtukan.org

http://www.freebirtukan.org
616.597.1086
PO Box 3158, Cypress, CA 90630
admin@freebirtukan.org

# Free Birtukan and all prisoners of Conscience in Ethiopia

ሚያዝያ 25  2002 ዓ.ም.

## ብርቱካን ሚደቅሳ የልጆቻችንም «እናት» ናት!

በሰሜን አሜሪካ በየአመቱ ከሚከበሩ፣ ሌሎች አገራትም ሊከተሉት ከሚጋባቸዉ ክብረ በዓላት መካከል "የእናቶች ቀን" አንዱ ነዉ። በዚህ አመት የእናቶች ቀን እሁድ ግንቦት 2 ቀን (ሜይ 9 ) ይከበራል። ይህ ቀን ዘጠኝ ወራት በማህጸናቸው ተሸክመውና ወልደው ያሳደጉ እናቶቻችንን «እግዚአብሄር ይስጥልኝ» የምንልበትና አክብሮታችንን የምንገልጽበት ቀን ነዉ። በመሆኑም በመላው አለም የሚገኙ እናቶችን "እንኳን ለእናቶች ቀን በሰላም አደረሳችሁ" ስንል፤ እንደ ብርቱካን ሚዴቅሳ ሁሉ ያለፍትህ የታሰሩትን እናቶች በማስታወስ ነው።

ብርቱካን ሚዴቅሳ በአገር ሽምግልና ወግ፤ በነሐሴ ወር 1999 ዓ.ም. ከቃሊቲ ወህኒ ቤት በወጣች ማግስት፤ የአንድ ልጇንና የወላጅ እናቷን ናፍቆት ሳትጨርስ፤ ለአገሯ፣ ለህዝቧና ለፓርቲዋ ልዕልና ስትል ነበር... በሰላማዊ መንገድ ህዝባዊውን ትግል የተቀላቀለችው። ለዚህም ክቡር አላማ ከአገር ቤት አንስታ፤ ወደ አሜሪካ እና አውሮፓ በመሄድ ሰላምንና ፍቅርን ስትሰብክ ቆየች። በአገራችንም ታሪክ የመጀመሪያዋ የፖለቲካ ድርጅት መሪ በመሆን ታሪካዊ የሰላም ገድል ማስመዝገብ ጀመረች። ይህ የፍትህና የአንድነት ጠበቃ መሆኗም ዳግም ወደ ቃሊቲ እስር ቤት እንድትወረወር ምክንያት ሆነ።

በመሆኑም ከአሥራ ስድስት ወራት በኋላ በታህሳስ 2001 ዓ.ም.፣ ይህች የሰላም እናት ከልጇ፣ ከወላጅ እናቷ፣ ከፓርቲዋና ከሚወዳት ህዝብ ተለየች። "ይቅርታ አልጠየኩም ብለሻል" በሚል የሃሰት ክስ ተመስርቶባት፣ በስድስት የደህንነት አባላት እየተገፋች ዳግም ወደ ቃሊቲ እስር ቤት ወረደች። በታሰረችበት ምሽትም የእድሜ ልክ እስራት ፀናባት። ለመቶ ሰማኒያ ቀናት ልጇን እንዳታይ ተከልክላ በጨለማ ቤት ዉስጥ፤ በነፈሰ ገዳዮች ላይ እንኳን ባልደረሰ መልኩ የስነ ልቦና ቶርቸር ደርሰባት።

ስፍር ቁጥር የሌላቸው ኢትዮጵያዉያን፣ የዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾችና፣ የዉጭ መንግስታት ባለስልጣናት መፈታቷን ቢጠይቁም፣ በኢትዮጵያ የሚገዙ ባለሥልጣናት፤ ልባቸውን አደንድነውና ጨክነው፤ ይህችን የሰላም እናት ዛሬም በእስር ቤት እንድትማቅቅ አድርገዋል። እንቅልፍ መተኛት እስኪያቅታት ድረስ በከፍተኛ ሕመም ላይ ናት ያለችዉ። ሕመሟን በተመለከተ በማረሚያ ቤት ያሉ ሃኪሞች ምንም ማድረግ ባለመቻላቸዉ ገለልተኛ በሆኑ ሐኪሞች እንድትታይ ብትጠይቅም፣ በጭካኔ የተሞሉት ባለሥልጣናቱ፣ ወ/ት ብርቱካን በሕዝብ ዘንድ ባላት ከፍተኛ ድጋፍ በመናደዳቸዉ በዚች ታላቅ ሴት ላይ አሁንም ከፍተኛ ግፍ በመፈጸም ላይ ይገኛሉ።

ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ የሕሊና እሥረኛ እንጂ የሕግ እሥረኛ አይደለችም። ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ለፍትህ የቆመች ሴት እንጂ ወንጀለኛ አይደለችም። ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ በኢትዮጵያ ሕግ የበላይ ሆኖ፣ መልካም አስተዳደር ሰፍኖ ፣ የዜጎች መብት የተከበረባት፣ አንድነቷ የተጠበቀ አንዲት ኢትዮጵያን ለመገንባት የሚደረገውን ህዝባዊ እንቅስቃሴ ስትመራ የነበረች የዘመናችን ታላው ሴት ናት። ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ የሃሌ እናት ትሁን እንጂ፤ እንደ ሃሌ ላሉት በሚሊዮኖች ለሚቆጠሩ የኢትዮጵያ ልጆች የበለጸገች አገር ለመተዉ ብላ ነዉ የታሰረቻዉ። ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ የሃሌ ሚደቅሳ ብቻ ሳትሆን፤ የመጪው ትውልድ የክብር እናታቸው ናት።

http://www.freebirtukan.org
616.597.1086
PO Box 3158, Cypress, CA 90630
admin@freebirtukan.org

# Free Birtukan and all prisoners of Conscience in Ethiopia

**ሚያዝያ 25 2002 ዓ.ም.**

በመሆኑም በዚህ በእናቶች ቀን፣ በዚህ አሳዛኝና አስከፊ ሁኔታ ውስጥ ያለችውን ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳን፣ ሁላችንም እንድናስባት ጥሪ እናቀርባለን። ትፈታም ዘንድ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ የድርሻውን እንዲወጣ፣ ላሰሯት ግለሰቦች እርሷን አስረው በሰላም መኖር እንደማይችሉ፣ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ደጋፊዎችና አፍቃሪዎች እንዳሏት የሚገልጽ መልእክት እንዲደርሳቸው መደረግ አለበት።

“የብርቱካን ትፈታ” ግብረ ኃይል፣ የኢትዮጵያ ሴቶች ለሰላምና ለዕድገት ድርጅት፣ እንዲሁም ሌሎች ድርጅቶች በመተባበር በእናቶች ቀን ፣ ወ/ት ብርቱካን ሚዴቅሳን ለማስታወስ አርብ ሚያዚያ 29 ቀን (ሚይ 7) በዋሺንግተን ዲሲ ስቴት ዲፓርትሜንት ከጠዋቱ 9 ሰአት ሰላማዊ ሰልፎች አዘጋጅተዋል። በዋሺንግተን ዲሲ ዙሪያ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ሁሉ፤ በዚያ ቀን ተገኝተው ለዚች ታላቅ ኢትዮጵያዊት እናት ያላቸውን የትግል አጋርነትና ፍቅር እንዲገልጹ በአክብሮት እንጠይቃለን።

ደቡብ አፍሪቃውያን ማንዴላ ሲታሰር ዝም አላሉም። ሕንዶች ጋንዲ ሲታሰር እጃቸውን አጣጥፈው አልተቀመጡም። መሪው ከፊት ቀድሞ ሲሰዋ፣ መሪውን ተከትሎ ለመሪው ያልቆመ ሕዝብ፣ መሪውን አስበልቶ ወደ ኋላ የሚሸሽ ሕዝብ ነጻ ሊወጣ አይችልም። ሰላማዊው የነጻነት ጉዞ ብርቱካን ሚደቅሳን በማስፈታት ነው የሚቀጥለው። በመሆኑም ሁሉም ኢትዮጵያዊ እንደየሃይማኖቱ፤ በሚቀጥለው አርብ ቀን ሙስሊም ወገኖቻችን በመስኪዶች፣ እሑድ ደግሞ የክርስትና እምነት ተከታዮች በየአብያተ ክርስቲያናቱ ለወ/ት ብርቱካንና እንደሷ ያለፍትህ የታሰሩ ኢትዮጵያዊያንን በህሊና ፀሎት እንዲያስቧት፤ ም ዕመናንና የሃይማኖት አባቶችን እንጠይቃለን።

በዚህ አጋጣሚ በአሜሪካና በካናዳ የምትኖሩ ወገኖቻችን በተለይም እናቶች፣ ለነኝህ አገሮች መሪዎችና ሕገ አውጭ በለስልጣናት የተዘጋጁ ደብዳቤዎችን ከድረ ገጻችን በመውሰድ፣ በደብዳቤም ሆነ በኢሜል በመላክ፣ ወ/ት ብርቱካን በአስቸኳይ ህክምና እንድታገኝና ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ከእስር እንድትፈታ ለሚደረገው ጥረት ተባባሪ እንድትሆኑ በአክብሮት እንጠይቃለን።